# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 356 የካቲት 28 2007 ገጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ታላቁን የአድዋን ድል ለአጎናፀፉን ቀደምቶቻችን ያለንን ክብር መግለጽ ያለብን ዛሬ አገራችን ከህወሓት የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በምንገባው ቃል ኪዳን ነው ብሎ ያምናል።

አርበኞች ግንቦት 7: የአድዋ ድልን እያከበርን ዛሬ ነፃነታችንን ለማስከር ለመታገል ቃል እንግባ ይላል።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ ሰማያዊ ፓርቲ የቅስቀሳ መልእክቱን ለዉጥ ብሎ አስገደደ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ፣ ኤፍ ኤም 96.3፣ ሰማያዊ ፓርቲ ለምርጫ ቅስቀሳ ያቀረባቸውን መልእክቶች እንዲለውጥ፣ ካልለወጠ ግን እንደማያስተላልፍ ገለጸ። ጣቢያው እንዲወጡ ከጠየቃቸው መልእክቶች መካከል “ሀገራችን ዛሬ በቀሪው ዓለም የምትታወቀው በእርስ በርስ ጦርነት ነው” የሚለው የሚገኝበት ሲሆን፣ መልእክቱ ለአመጽና ለሁከት የሚያጋልጥ ነው የሚል ምክንያት አቅርቧል። ሌላው እንዲወጣ የተጠየቀው “ህዝቧ የዘር፣ የኃይማኖት፣ የቋንቋና የባህል ልዩነቶችን ተቀብሎ ለበርካታ ዘመናት ተቻችሎ የኖረ ቢሆንም ዛሬ ግን እርስ በርስ በጥርጣሬ እንዲተያይና አንድነቱ እንዲላላ እየተደረገ ነው” የሚለው መልእክት ሲሆን፣ መልእክቱ ብሔር፣ ብሔረሰቦችን የሚያጋጭ ወይንም የእርስ በርስ ግጭት የሚያስነሳ፣ አመፅና ጦርነት የሚቀሰቅስ ነው ተብሏል።

ዝግጅቱ የታጀበበት ሙዚቃ የድምጻዊውን ፍቃድ መያዝ እንዳለበትም የሬዲዮ ጣቢያው ለመስተዳድሩ በላከው ደብዳቤ ላይ ጠቅሷል።የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ዮናታን ተስፋዬ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ የቅስቀሳ ፕሮግራሙ ውስጥ እንዲስተካከሉ የላካቸው ሀሳቦች የሰማያዊ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ያፀደቃቸው፣ የፓርቲው ፕሮግራም አካልና ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም የተቀበላቸው መሆናቸውን በመጥቀስ፣ ራዲዮ ጣቢያው በፓርቲው የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ቅድመ ምርመራ እያደረገ ነው ሲሉ ለነገረ ኢትዮጵያ ገልጸዋል። ...... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ም/ል ጠ/ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው

የቅዱስ ጊዮርጊስ እና የአልጀሪያው ኤል ኡልማ ቡድኖችን ጨዋታ ለማየት በባህርዳር ስታዲየም በእንግድነት የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር ደመቀ መኮንን ከጨዋታው በፊት ንግግር እንዲያደርጉ በተጋበዙበት ሰአት ጨዋታውን ለመመልከት በስቴዲየሙ የተገኘው ሕዝብ በታላቅ ቁጣ የተቃውሞ ድምጽ በማሰማቱ ንግግራቸውን እንዲያቋርጡ መገደዳቸውን የክልሉ ወኪላችን ገልጻለች። አብዛኛው ህዝብ ከተቃውሞ ድምጹ ጋር የተቀናቃኝ ፓርቲዎችን የምርጫ ምልክት በእጁ በማሳየት አቶ ደመቀ ንግግራቸውን እንዲያቋርጡ አስገድዷቸዋል። የጊዮርጊስ ጨዋታ ወደ ባህርዳር የተላለፈው የህወሃት 40ኛ አመት ዝግጅትን ለማካሄድ ሲባል አዲስ አበባን ከሁሉም ትኩረት ከሚስቡ ነገሮች ነጻ በማድረግ ነዋሪው በሙሉ ልቡ የዕለቱን ዝግጅት በቴሌቪዥን መስኮት እንዲመለከት በማሰብ እንደሆነ ከአዲስ አበባ ቡድናቸውን ለመደገፍ የመጡ ተመልካቾች ለዘጋቢያችን ገልጸውላታል። በተሰጠው አስተያየት ዙሪያ የፌደሬሽኑንመ አስተያየት ለማግኘት ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም።

## ወያኔ በምርኮኛ ወታደሮች የመሰረተው ኦህዴድ 25ኛ ዓመቱን ሊያከብር ነው

የቀድሞ የደርግ ወታደሮችን በማሰባሰብ በህወሃት በጎ ፈቃድ የተመሰረተው የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) የተመሠረተበትን 25 ዓመት በድምቀት ለማክበር መዘጋጀቱን አስታውቋል። የኦህዴድ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ዳባ ደበሌ በሰጡት መግለጫ ኦህዴድ የተመሰረተበትን 25ኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ በዓል ከመጋቢት 1 እስከ መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም በልዩ ልዩ መርሃግብሮች ያከብራል። በወጣው ፕሮግራም መሰረትም ከመጋቢት 1 እስከ 16 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ .ባሉት ጊዜያት በክልሉ የሚከናወኑ የልማት ስራዎችን ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ህዝባዊ ንቅንቄ ለማድረግ ያስችላሉ የተባሉ የፓናል ውይይቶች፣ ሕዝባዊ ሰልፎች እንደሚካሄዱና መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም ዋናው በዓል እንደሚከበር አስታውቀዋል። .... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ሱዳናዊዉ ሹፌር በጩቤ ወግቶ ከመኪና የወረወራት ኢትዮጵያዊ ከዚህ አለም በሞት ተለየች

ባለፈዊ የካቲት 24፣ 2007 ዓም በሱዳናዊዉ ሹፌር በአሰቃቂ ሁኔታ ጥቃት የተፈጸመባት ኢትዮጵያዊት ወጣት ከዚህ አለም በሞት መለየቷን የአካባቢው ነዋሪዎች ተናግረዋል። አንድ የሱዳን ታርጋ ያለው፣ በሱዳናዊ ሹፌር የሚሽከረከር ማዳበሪያ ያጫነ ከባድ መኪና ከሱዳን ወደ ባህርዳር በመጓዝ ላይ እንዳለ እንፍራዝ እየተበላ የሚጠራ አነስተኛ ከተማ ላይ ሲደርስ ጥብብር ጠይቃዉ የጫናትን ኢትዮጵያዊት ወጣት በስለት ወግቶ ሁለት አይኖቿን ካወጣና ከፍተኛ ጉዳት ካደረሳባት በኋላ ከመኪናዉ ጎትቶ እንደጣላት መዘገቡ የሚታወስ ነዉ። ሾፌሩ እንዲህ አይነቱን አሰቃቂ ወንጀል ለምን ሊፈጽም እንደቻለ የተለያዩ መረጃዎች ቢሰጡም ብዙዎችች እንደሚሉት የወንጀሉ መነሻ ሱዳናዊዉ ሾፌር ወጣቷን ሊደፍራት ሲሞክር በተፈጠረ አለመግባባት ነዉ። ድርጊቱ ሲፈጸም በሩቁ ያየ አንድ የሌላ መኪና አሽከርካሪ ወደ ወረታ በመጓዝ ላይ የነበረ ሌላ መኪና አስቁሞ ወጣቷን ወደ ህክምና ቦታ እንድትወሰድ ካደረገ በኋላ፣ ሹፌሩ ወንጀከል ፈፃሚዉን ሾፌር ተከታትሎ ጉዳዩን ለፖሊሶች ሪፖርት ካደረገ በኋላ፣ ፖሊሶች ሹፌሩን ጉማራ ላይ እንዲያቆም ሲጠይቁት፣ ሹፌሩ ፈቃደኛ ሳይሆን ጥሏቸዉ ማለፉ ታዉቋል። ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የአድዋ ድል በአል በተለያዩ የአለም ከተማዎች በድምቀት ተከበረ

ኢትዮጵያውያን የጣሊያንን ወራሪ ሃይል ድል የመቱበትና ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቁሮች በነጮች ላይ የአሸናፊነት ታሪክ የጻፉበት የአድዋ ድል 119 አመት በአል በአዲስ አበባ ተከብሮአል። በርካታ አርበኞችና ወጣቶች፣ የአድዋን ድል በመሩት በአጼ ሚኒሊክ ሃውልት ዙሪያ በመሰባሰብ ቀኑን አክበረው የዋሉ ሲሆን ወጣቶች የጀግንነት መገለጫ የሆነውን ባህላዊ ሽለላ ሲያሰሙ፣ ባልተጠበቀ ሁኔታ በፖሊስ እንዲበተኑ ተደርጓል። ፖሊሶች ያልተፈቀደ ሰልፍ ነው በማለት ወጣቶችን መበተናቸውን በስፍራው የነበረው የኢሳት ወኪል ቀርጾ ከላከው ቪዲዮ ለመመልከት ይቻላል።

የዛሬ 119 ዓመት በጄ/ል ባራቴሪ የተመራው የጣሊያን ጦር ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎችን ታጥቆ መላ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ህልም የነበረው ቢሆንም፣ በአጼ ሚኒሊክና በባለቤታቸው በእቴጌ ጠሃይቱ የተመራው ጦር፣ ከአዲስ አበባ ገስግሶ በመሄድ የጣሊያንን ወረራ በማክሸፍ፣ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቁሮች ነጮችን ድል ያደረጉበትን ታሪክ አስመዝግቧል። የአድዋን ድል ተከትሎ በጣሊያን የጠ/ሚኒስትር ክርስፒ መንግስት ፈርሷል። አውሮፓውያን ደግሞ ኢትዮጵያን እንደ አንድ ነጻ አገር እንዲቆጥሩ ተገደዋል። ድሉ በመላው የጥቁሮች ዘር የፈጠረው ስሜት በሁዋላ ላይ ለታዩት የጸረ ቅኝ ግዛት ትግሎች ከፍተኛ እገዛ አድርጓል። በእለቱ በተደረገው ጦርነት በሺዎች የሚቆጠሩ ጣሊያውያን ሲገደሉ፣ ብዙዎችም ተማርከዋል። በኢትዮጵያ በኩልም በሺዎች የሚቀጠሩ ዜጎች መስዋት ሆነዋል። ...... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የብረታብረት ኢንዱስትሪዎች ለኪሳራ መዳረጋቸው ተገለጸ

የብረታብረት ኢንዱስትሪዎች ከኃይል አቅርቦት መቆራረጥ፣ ከአቅርቦት ማነስ እንዲሁም ከውጪ ምንዛሪ እጥረት ጋር ተያይዞ በሙሉ አቅማቸው ማምረት አለመቻላቸውና ለኪሳራም እየተዳረጉ መሆናቸውን መረጃዎች አመልክተዋል። የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሰሞኑን በግዮን ሆቴል የ2007 ግማሽ ዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለባለድርሻ አካላት ባሳወቀበት ወቅት እንደተጠቀሰው በብረታብረት ዘርፍ ወደ 60 የሚሆኑ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ኢንዱስትሪዎች በዋንኛነት ከኃይል አቅርቦት መቆራረጥና ከአቅርቦት ማነስ ጋር ተያይዞ ከማምረት አቅማቸው እያመረቱ የሚገኙት 41 በመቶ ያህል ብቻ ነው።

አንዱስትሪዎቹ በጠቅላላው 129 ነጥብ 6 ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ያላቸው ቢሆንም መንግስት በትክክል ማቅረብ የቻለው 69 ነጥብ 6 ሜጋዋት ብቻ ነው። ፋብሪካዎቹ ቀሪ 60 ሜጋዋት ገደማ የኃይል አቅርቦት ክፍተት እንዳለባቸውና ይህም ችግር መቼ እንደሚፈታ እንደማይታወቅ ተጠቁሞአል። እነዚህ ፋብሪካዎች የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በማሟላት ለኢክስፖርት እንዲያመርቱ በመንግስት በኩል ፍላጎት ቢኖርም በዋንኛነት ከኃይል አቅርቦት ጋር ተያይዞ ይህ ሊሳካ እንዳቻለ ታውቋል።

## የአድዋ ድልን እያከበርን ለዛሬ ነፃነታች ቃል እንግባ !

መቶ አስራ ዘጠነኛውን የአድዋ ድል በዓል እየዘከርን እንገኛለን። እንደዛሬው ሁሉ ያኔም ቀደምቶቻችን በርካታ የውስጥና የውጭ ችግሮች ነበሩባቸው። እንደዛሬው ሁሉ ያኔም በመካከላቸው የሀሳብና የጥቅም ልዩነቶች ነበሩ። ያም ሆኖ ግን ቀደምቶቻችን በአገር ነፃነት ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ መግባባት ላይ መድረስ በመቻላቸው በዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችና ድርጅት የተጠናከረውን የአውሮፓ ጦር በጥቁር የጦር አዛዦችና ተዋጊዎች መመከት ቻሉ። ከአድዋ በፊት አፍሪቃ በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ አውሮፓዊያን የተሸነፉባቸው ተናጠል አውደ ውጊያዎች ነበሩ፤ ጦርነትን ሲሸነፉ ግን አድዋ የመጀሪያው ነው። በዚህም ምክንያት ነው የአድዋ ድል የአፍሪቃውያን ከዚያም አልፎ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ድል ተደርጎ የሚወሰደው።

ዛሬ ግን እኛ ያኔ የነበሩት አያትና ቅድመ አያቶቻችን እደረሱበት የመግባባት ደረጃ ላይ መድረስ ባለመቻላችን አገር በቀሉን ቅኝ ገዢ - ህወሓትን - ከኢትዮጵያዊያን ጫንቃ ላይ ማውረድ አቅቶን አገራችንና ሕዝቧን ከባዕድ በባሰ ሁኔታ እያዋረደ በመግዛት ላይ ይገኛል።

ያኔ ለሀገሩ፣ ለነፃነቱና ለክብሩ ቀናዒ የሆነው ኢትዮጵያዊ ራሱን ወታደር አድርጎ በየጎበዝ አለቃው አዝማችነት በጠላት ላይ ዘምቶ ድልን ተቀዳጅቷል። ዛሬ ግን ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ የመከላከያ ሠራዊት አባል ለህወሓት አዛዦች ሎሌነት አድሮ የራሱን ወገን ይፈጃል። ያኔ በአገዛዙ ላይ ብሶት የነበረው እንኳን ሳይቀር ብሶቱን ችሎ ለሀገር ሉዓላውነትና ክብር ሲል ተዋድቋል። ዛሬ ግን ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ወገኖቻችን የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም ከብሶቶቻቸው በላይ አሻግረው መመልከት ተስኗቸዋል።

ዛሬ 119ኛውን የአድዋ ድል በዓል አያቶቻችንን በማድነቅ ብቻ ልናሳልፈው አይገባም። የአያቶቻችንን ገድል ስናከብር ዛሬ የምንገኝበትን ሁኔታ መመዘን ይገባናል። ራሳችንን ከእነሱ ጋር በማስተያየት እንደምን ያለን ውለታ መላሽ ያልሆንን የልጅ ልጆች መሆናችንን መመዘን እና ራሳችንን መውቀስ ይገባናል። የሚያሳዝነው ዛሬ ራሱን ከሚወቅሰው በላይ አያቶቹን የሚወቅስ መብዛቱ ነው። እነሱ ችግሮችን ተሻግረው የምንኮራበትን ድል አቀዳጅተውን አልፈዋል። እኛ ግን እነሱ ያቆዩልንን ድል እንኳን ማስጠበቅ አልቻልንም። ከአድዋ ድል አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ ዓመታት በኋላ አገራችንን ለህወሓት የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ማስረከባችን ሊያመንና ሊያንገበግበን ሲገባ ድሮ ሊደረጉ ሲችሉ አልተደረጉም በምንላቸው ነገሮች ላይ እየተከራከርን ግዜያችንን እናጠፋለን።

አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ታላቁን የአድዋን ድል ለአጎናፀፉን ቀደምቶቻችን ያለንን ክብር መግለጽ ያለብን ዛሬ አገራችን ከህወሓት የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በምንገባው ቃል ኪዳን ነው ብሎ ያምናል። አገራችንን በቅኝ ግዛትነት እያስገዛን የቀደምቶቻችንን ድል መዘከር ለእኛ ለልጆቻቸዉ የሚያሳፍር ተግባር ነው ብሎ ያምናል። አርበኞች ግንቦት 7 የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አገር በቀል ቅኝ ገዥ በሆነው ሕወሓት እየተመራ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማዳከሙን ተግባር በአስቸኳይ ማቆም ይኖርበታል ብሎ ያምናል። ስለሆነም የመከላከያ ሠራዊት አባላት ልባችሁንም ክንዳችሁንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አድርጉ። ቀደምት አባቶቻችን አድዋ ላይ ድል የነሱት ቅኝ ገዥ ዛሬ ቀለሙን ለውጦ "ህወሓት" ተሰኝቶ ያንተ አዛዥ ሆኗል። መሣሪያህን በህወሓት አዛዦችህ ላይ የምታዞርበት ወቅት አሁን ነው።

ንቃ፤ ተነስ !

አገርን ለጠላት አስረክቦ በቀደምት ጀግኖች ታሪክ መኩራት አሳፋሪ ነው። አባቶቻችን በነፃነት ያቆዩልን አገር የህወሓት መፈንጫ ሆና ማየት የሚያሸማቅቅ ነው። የጀግኖች አያቶቻችን የልጅ ልጆች መሆናችንን የምናስመሰክረው አገራችንን ከህወሓት አገዛዝ ነፃ ስናወጣና የዜጎቿ መብቶች የተከበሩባት ፍትህና እኩልነት የሰፈኑባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ስንመሠርት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ታላቅ ዓላማ ይነሳ ሲል አርበኞች ግንቦት 7 ጥሪ ያስተላልፋል።

አርበኞች ግንቦት 7: የአድዋ ድልን እያከበርን ዛሬ ነፃነታችንን ለማስከር ለመታገል ቃል እንግባ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ወያኔ ሰማያዊ ፓርቲ የቅስቀሳ መልእክቱን ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሙዚቃውን በተመለከተም "መብቱ የሙዚቀኛው እንጂ የራዲዮ ጣቢያው አይደለም። ሙዚቀኛው ደስተኛ ካልሆነ ካስተላለፍነው በኋላ ሊከሰን ይችላል። በዚህ ጉዳይ ጣቢያው የሚያገባው ነገር የለም" ሲሉ መልስ ሰጥተዋል። "በሚናገሩት ቋንቋ መነሻነት ብዙ ዜጎች በተደጋጋሚ ከቀያቸው እንደሚፈናቀሉ፣ በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ባለው ዘርን ያማከለ ሹመት ምክንያት በርካቶች የጎሪጥ እንደሚተያዩ፣ የጎሳ ፌደራሊዝሙ ለተደጋጋሚ ግጭት መዳረጉን መንግስት በሚያሰራቸው ጥናቶችም ጭምር መረጋገጡን የገለጹት የሰማያዊ ፓርቲ ም/ ሊቀመንበርና የምርጫ ጉዳይ ኃላፊው አቶ ስለሽ ፈይሳ፣ ራዲዮ ጣቢያው የቅስቀሳ ፕሮግራሙ ላይ እንዲቀየሩ የጠየቃቸው ሀሳቦች በመረጃ የተደገፉ ናቸው ሲሉ ለጋዜጣው ተናግረዋል። አቶ ስለሽ አክለውም "ሰማያዊ ፓርቲ ፕሮግራሙ ላይ ያለውን ሀሳብ አውጣ እየተባለ ቅድመ ምርመራ ሲደረግበት፣ ኢህአዴግ ግን ተቃዋሚዎችን "ህገ-ወጥ" ከሚላቸው አካላት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው እየከሰሰና እያንቋሸሸ ቅስቀሳ እያካሄደ ነው። ይህ ደግሞ ራዲዮ ጣቢያው በግልጽ አድሎአዊነቱን እያሳየ እንደሆነ ትልቅ ማስረጃ ነው" ሲሉ አክለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሰማያዊ ፓርቲ ዛሬ በአዲስ አበባ በጀመረው ይፋ የምርጫ ቅስቀሳ አባላቱ ሲታሰሩ አንድ የፓርቲው አመራር አባል ደግሞ በአማራ ክልል ከተሞች ልማትና ግንባታ ውስጥ ከነበራቸው ኃላፊነት ተነስተዋል። ሰማያዊ ፓርቲ እንዳስታወቀው ዛሬ ከማለዳ ጀምሮ በአዲስ አበባ በሁሉም ክፍለ-ከተሞች በመዟዟር የምርጫ ቅስቀሳ በይፋ ጀምሯል። ይሁንና በቅስቀሳ ሥራ ላይ የነበሩ ሁለት የፓርቲው አመራሮችና ሌሎች አባላትም ረፋዱ ላይ ከሽሮሜዳ አካባቢ በፖሊስ ታፍነው መወሰዳቸውን ፓርቲው አስታውቋል። ታፍነው ወደ "ላዛሪስት" ፖሊስ ጣቢያ የተወሰዱት የፓርቲው አመራሮች፡- የምርጫ ክልል 12/13 እጩ የሆነው ዶ/ር ዘላለም ደሳለኝ እና የምርጫ ክልል 10 እጩ የሆነው አቶ ይድነቃቸው አዲሱ ናቸው። ከነሱ ጋር አብረው የነበሩት የቅስቀሳ ቡድኑ አባላት አቶ ሳምሶን ግዛቸው፣ ወ/ሪት ምዕራፍ ይመር፣ አቶ ፍሬው ተክሌ ፣ የቴክኒክ ባለሙያዎች፣ ሹፌሩና ረዳቱም አብረው መታሰራቸውን ፓርቲው አስታውቋል። በፖሊሶች በታገተው መኪና ውስጥም ከአስር ሺህ በላይ በራሪ ወረቀቶች አብረው መታገታቸውንም ሰማያዊ ፓርቲ አመልክቷል። ይህ በ እንዲህ እንዳለ የአማራ ክልል ከተሞች ልማትና ግንባታ፤ የሰማያዊ ፓርቲ የምዕራብ ጎጃም ዞን ተወካይ እንዲሁም የምዕራብ ጎጃም፣ ምስራቅ ጎጃምና አዊ ዞን የምርጫ ግብረ ኃይል አባል የሆኑትን አቶ አዲሱ ጌታነህን "ማኔጅመንቱን ያውካል፣ የስራ ተነሳሽነት የለውም" በሚል ከኃላፊነታቸው እንዳነሳቸው በደብዳቤ አሳውቋል። መስሪያ ቤቱ አቶ አዲሱ ጌታነህን "ባሳዩት ብቃት" በሚል የዛሬ አምስት ወር፤ ማለትም ጥቅምት 23 2007 ዓ.ም አሁን በሻራቸው የኃላፊነት ቦታ ላይ እንደመደባቸው ከቢሮው የወጣው የምደባ ደብዳቤ ያመለክታል። በብቃት ሀላፊነት ላይ በመደባቸው በአምስት ወር ጊዜ ውስጥ፣ "ማኔጅመንቱን ያውካል፣ የሥራ ተነሳሽነት የለውም" በማለት የወሰደባቸውን እርምጃ እንደማይቀበሉት የገለጹት አቶ አዲሱ፤ የተወሰደባቸው እርምጃ ፖለቲካዊ መሆኑን ተናግረዋል። አቶ አዲሱ አክለውም "ባህርዳር ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ኃይል እየተፈጠረ ነው። በተለይ የአንድነት መዋቅር ሰማያዊን ከተቀላቀለ በኋላ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ ይገኛል። ይህንም ተከትሎ የተለያዩ አገራት አምባሳደሮች ጋር ያደረግናቸው ውይይቶች ብአዴንን አስደንግጦታል" ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የምዕራብ ጎጃም ዞን የሰማያዊ ፓርቲ መዋቅር በአካባቢው ህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል፣ እንዲሁም ምርጫ ቦርድ ከዕጩ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚፈጥራቸውን ችግሮች ለሚዲያ እያጋለጡ መሆናቸው ከኃላፊነታቸው ለመነሳት አንድ ምክንያት እንደሆነ ተናግረዋል። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ አብዛኞቹ የአማራ ክልል ከተሞች ልማትና ግንባታ የቦርድ አባላት የብአዴን ከፍተኛ አመራሮች ናቸው።ከእነዚህም መካከል የባህርዳር ከተማ ከንቲባ አቶ ላቀ አያሌው፣ የክልሉ ም/ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ያለው አባተ እና የክልሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ኃላፊ አቶ አየነው ይገኙበታል። ከጥቂት ወራት በፊት በኢትዮጵያ አየር መንገድና በንግድ ባንክ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች በተመሳሳይ መንገድ ከስራቸው እንዲባረሩ መደረጋቸው አይዘነጋም።

# የኢትዮጵያ ጠላት ወያኔ - ወያኔ ብቻ ነዉ!

ባለፈዉ ሳምንት አይጋፎረም የሚባለዉና የወያኔን ቱልቱላ በዉጭ አገሮች የሚያናፍሰዉ ድረገጽ ከነብስ አባቱ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ በአደራ የተሰጠዉን አንድ የመላምት ድርሰት የፊት ለፊት ገጹ ላይ ለጥፎት የህዝብን ስሜት የኮረኮረ እየመሰለዉ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ ከሁለት ሺ አመታት በኋላ ይሁዳዊ ክህደት ሲከድ እጅ ከፍንጅ ተይዟል። የሚገርመዉ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር ሆኖ ሳለ ያንን የመሰለ የክህደት መንፈስ ልቡ ዉስጥ ያስቀመጠለት ሰይጣን እንደሆነ ሁሉ አዲስ ዘመንና አይጋ ላይ የወጣዉን ጽሁፍ የጻፈዉ ግለሰብም የወያኔ ጌቶቹን ምክር ተቀብሎ አሜን አለ እንጂ የዚህ የዉሸት ድርሰት ጠንሳሾች በሰይጣን የሚመሰሉት የወያኔ መሪዎች ናቸዉ። የጽሁፉ ደራሲ ነኝ ግለሰብ የወያኔን ትዕዛዝ ከመቀበል ዉጭ ያደረገዉ ነገር ቢኖር ስሙ ከፅሁፉ አርዕስት ስር እንዲቀመጥ መፍቀዱ ብቻ ነዉ - ለዚያዉም የብዕር ስም!

አገሮች፤ ድርጅቶች ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ዉስጥ ሲገቡ በዉሸት ዉስጥ እዉነት ወይም በእዉነት ዉስጥ ዉሸት እየሸነቆሩ ነዉ የፕሮፓጋንዳቸዉ ኢላማ የሆነዉን የህብረተሰብ ክፍል ቀልብ ለመግዛት የሚፍጨረጨሩት እንጂ ዉሸትን በዉሸት ለዉሰዉ ቢያቀርቡማ ህዝብ እንኳን ሊያምናቸዉ ደግሞ ሊሰማቸዉም ፈቃደኛ አይሆንም። ይህ ከሰሞኑ አይጋፎርምና አዲስ ዘመን ላይ የወጣዉ ጽሁፍ ግን ምንም አይነት የፕሮፓጋንዳ ህግ አይከተልም፤ ምክንያቱም ጽሁፉ የተጻፈዉ ህግ የሚባል ነገር በሌለባትና ወያኔና ግብረ አበሮቹ እራሳቸዉ ህግ በሆኑበት አገር ዉስጥ ነዉ። ጽሁፉ ሲጀምር በዉሸት ይጀምርና መሀል ላይ ዉሸቱን በዉሸት አጠናክሮ በዉሸት ይደመድማል። እንደዚህ አይነት የዉሸት ክምር የሚመጣዉ ደግሞ ከሌላ ከየትም ሳይሆን በዉሸት ተወልደዉ፤ በዉሸት አድገዉ በዉሸት ከሸበቱት የወያኔ መሪዎች ብቻ ነዉ። ዉድ አድማጮቻችን የዚህ ጽሁፍ አላማ ለሻዕቢያ ጥብቅና መቆም አይደለም፤ ሻዕቢያ ከኛ በላይ ለራሱ ጥብቅና መቆም ይችላል። የዚህ ጽሁፍ ብቸኛ አላማ የኢትዮጵያ ህዝብ ገንበዙን፤ ሀብቱንና ጉልበቱን አስተባብሮ መዋጋት የሚገባዉ ቀንደኛ ጠላቱ ወያኔ መሆኑን መናገር ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ትናንት ሲከናዉን የምናዉቀዉንና አይናችን ፊት ተፈጽሞ ከ "ሀ" ወደ "ፐ" የተጻፈዉን ታሪክ ዛሬ ወያኔና ቡችሎቹ ከ "ፐ" ወደ "ሀ" ሲያነብቡትና የኢትዮጵያን ህዝብ ለማሳሳት ሲሞክሩ ዝም ብለን አንመለከትምና ይህንን የዉሸት ክምር ከመሰረቱ መናድ እንፈልጋለን።

ይህንን በዉሸት የተጀቦደ የወያኔ ቡትቶ እንዳለ ማቅረቡ የአድማጭን ጆሮ ማደንቆር ስለሚሆን አንሞክረዉም። ሆኖም ወያኔ በተከበበና አንድ እርምጃ ወደማይቀረዉ ዉድቀቱ በቀረበ ቁጥር የሚመዝዛቸዉን አገር የሚገዘግዙ መጋዞች የኢትዮጳያ ህዝብ ከአሁኑ አዉቆ እንዲጠነቀቅ ስለምንፈልግ የፅሁፉን ጎላ ጎላ ያሉ የዉሸት ምሶሶዎች እንዳሉ ለማቅረብ እንገደዳለን።

የመመሪያዉ አይን ያወጣ ዉሸት "በወቅቱ ኢሕአዴግ ከበረሀ ይዞት የመጣው መደበኛ ያልሆነ ሰራዊት ብቻ በእጁ ነበር። ቀድሞ የነበረው የኢትዮጵያ መከላከያ ሀይል፣ የምድር ጦሩ፣ ታንከኛው፣ መድፈኛው፣ አየር መከላከያው፣ አየርሀይሉ፣ ባህር ኃይሉ፣ ኮማንዶው ሰራዊት፣ ፖሊስና ሌሎችም ሙሉ በሙሉ ተበትነዋል" ይላል። ይህ ዉሸት ከተለመዱት የወያኔ ተራ ዉሸቶች ጋር ሲተያይ ተጠንቶበት በጥንቃቄ የተዋሸ ዉሸት ይመስላል። የቀድሞዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ወራዊት ሰራዊት አባላት በገዛ ፈቃዳቸዉ የተበተኑ ይመስል የዚህ ጽሁፍ ጸሀፊ የቀድሞዉ የመከላከያ ኃይል ሙሉ በሙሉ ተበትነዋል እያለ ነዉ የሚነግረን። በእርግጥም ቁጥሩ ከ300 መቶ ሺ በላይ የሚሆን ሰራዊት የኢትዮጵያ ሠራዊት መሆኑ ተረስቶ የደርግ ጦር፤ የትምክህተኞች ኃይል ወይም የነፍጠኞች ምሽግ እየተባለ በወያኔ ዘረኞች ተበትኖ በምትኩ በአንድ ዘር የበላይነት ላይ የተመሰረተ የመከላከያ ኃይል ተገንብቷል። የቀድሞዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የማን ሠራዊት እንደነበር፤ ለምንና በማን እንደተበተናና በምትኩም የተገነባዉ ሠራዊት ለማን ጥቅም እንደቆመ የኢትዮጵያ ህዝብ አንደ ጥቁር ነጭ ለያይቶ የሚያዉቀዉ ሀቅ ነዉና ከዚህ በላይ የምንለዉ ምንም አይኖርም።

ከአንድ ወር በፊት የኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቭዥንና ሬድዮ ጋዜጠኞች በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝብ መካከል ሊኖር የሚገባዉን ግኑኝነትና ኤርትራ ዉስጥ እየተካሄደ ነዉ የሚባለዉን የኢትዮጵያ ህዝብ የነጻነት ትግል እንቅስቃሴ አስመልክቶ እዉነቱን ለህዝብ ለማሳወቅ ታሪካዊ ጉዞ ወደ አስመራና የኤርትራ በረሀዎች አድርገዉ ነበር። በጉዟቸዉ ወቅት ጋዜጠኞቹ ሰፋ ያሉ ጉዳዮችን የዳሰሰ ቃለ መጠይቅ ከኤርትራዉ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር አድርገዉ ነበር። ይህ ማን ምን ሰራ የሚለዉን ጥያቄ በታሪክ ወደ ኋላ እየሄደ የሚመልሰዉና በአይነቱ ልዩ የሆነዉ የፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ቃለመጠይቅ በመገናኛ አዉታሮች መሰራጨት ሲጀምር የኢትዮጵያ ህዝብ ከደደቢት ዉሸትና ተረት ዉጭ ሌላ ሲሰማ የሚያመዉ ወያኔ እንደለመደዉ ሲወራጭና እዉነትን ለመጋረድ ሲፍጨረጨር ታይቷል።

የኢትዮጵያን ህዝብ እንዳሰኛቸዉ የሚረግጡት፤ የሚያስሩት፤ የሚገድሉትና በተለይ በቅርቡ የመስፋፋትና የማፈናቀል ፖሊሲያቸዉን የሚቃወመዉን ሁሉ "ልክ እናስገባዋለን" ብለዉ የዛቱት የወያኔ መሪዎች የእነሱን ጠላትነትና ስር የሰደደ ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ሸፍነዉ ኤርትራን የኢትዮጵያ ዋነኛ ጠላት አድርገዉ ማቅረብ ጀምረዋል። የሚገርመዉ ይህ ሁሉ አልበቃ ብሏቸዉ የፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ቃለ መጠይቅ በኢሳት ቴሌቪዥን በሚተላለፍበት ወቅት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በተለይ ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ ቀድሞዉኑም ከብልጭ ድርግም አልፎ የማያዉቀዉን አሌክትሪክ ጭራሽ እንዲጠፋ አድርገዋል።

ሻዕቢያና ህወሓት የትጥቅ ትግል በሚያካሄዱበት ግዜ የተነሱበትን ዋነኛ አላማ ለማሳካት የተለያዩ የፕሮፓጋንዳ ጨዋታዎችን ተጫዉተዋል። ከእነዚህ የፕሮፓጋንዳ ጨዋታዎች ዉስጥ አንዱ ኢትዮጵያ ኤርትራን በቅኝ ግዛትነት ይዛለች የሚለዉ ፕሮፓጋንዳ ነዉ።የሚገርመዉ ይህንን ፕሮፓጋንዳ ከባለቤቱ ከሻዕቢያ ይበልጥ የተሸከመዉና ያርገበገበዉ ህወሓት ህወሓት ዉስጥ ደግሞ መለስ ዜናዊና ስብሀት ነጋ ናቸዉ። ይህ ደግሞ ዛሬ እኛ ፈጥረን የምናወራዉ ወሬ ሳይሆን በቦታዉ የነበሩና ህወሓትን የፈጠሩት እን ገብሩ አስራትና እነ ገ/መድህን አርአያ በግልጽ የሚናገሩት እዉነት ነዉ። የትናንቱን የኢህአፓ የበረሃ ዉስጥ ታሪክ ትዝ ለሚለን ደግሞ ህወሓትንና ኢህአፓን ጦር አማዝዞ ለአያሌ ኢትዮጵያዉያን ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነዉ ኢህአፓ ይህንኑ የወያኔን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት የሚለዉን መዝሙር አልዘምርም በማለቱ ነበር። እንግዲህ ዛሬ ይህ ሁሉ መረጃና ይህ መረጃ በእጃቸዉ ላይ ያለ ሰዎች በህይወት እያሉ ነዉ የወያኔ አይነ አዉጣዎች "ከመጀመሪያዉም ሻዕቢያ እንደሚለፈልፈዉ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አልነበረችም፤ ይህ የእነ ኢሳያስ እብደት ነዉ እያሉ የራሳቸዉን ቀን የቆጠረ ዕብደት የሚነግሩን። በ1967 ዓም እግራቸዉ የደደቢት በረሃን ከረገጠበት ግዜ ጀምሮ በ1983 ዓም አዲስ አበባን እስከተቆጣጠሩበት ግዜ ድረስ በወዶ ገባነት ከገበቡበት ከሻዕቢያ ጉያ ያልተለዩትና አጠገባቸዉ ያለችዉን አክሱም ፅዮንን ትተዉ ሻዕቢያን ሲሳለሙ የከረሙት የወያኔ መሪዎች ዘንድሮ ሳይታሰብ በድንገት ቀኝ ኋላ ዙር ብለዉ ከሻዕቢያ ጋር የነበራቸዉን አለመግባባት መናዘዝ ጀምረዋል። በተለይ "ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት" ብለዉ እራሳቸዉ በጻፉት ማኒፌስቶ ዉስጥ ያሰፈሩትን ቃል ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የረሳ መስሏቸዉ የክህደት ጫጫታ መደርደር ጀምረዋል።

አገራችን ኢትዮጵያ በየዘመኑ በአንድነቷና በሉዓላዊነቷ ላይ የዘመቱ ብዙ ታሪካዊ ጠላቶች ነበሯት፤ ዛሬም አሏት፤ ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ በረጂም ዘመን ታሪኩ ዉስጥ እንደ ወያኔ ህልዉናዉን፤ አንድቱንና የወደፊት ተስፋዉን ያጨለመበት የዉጭም የዉስጥም ጠላት አጋጥሞት አያዉቅም። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች መብታቸዉ፤ ነጻነታቸዉና እኩልነታቸዉ ተከብሮ የኖሩበት ዘመን ባይኖርም ኢትዮጵያ እንደ ወያኔ ዘመን በዘር የተከፋፈለችበትና የመበታተን አደጋ ያጋጠማት ግዜ የለም። ዛሬ የኢትዮጵያን አንድነትና የህዝቦቿን መብትና ነጻነት መከበር አጥብቀዉ የሚሹ ወገኖች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሊዋጉት የሚገባ ብቸኛ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጠላት ወያኑ ወይም ህወሓት ነዉ። የኢትዮጵያህዝብ መከፈል የሚገባዉን መስዋዕትነት ከፍሎ ወያኔን በአጭር ግዜ ዉስጥ ካላስወገደ የአገራችን ህልዉና በቀላሉ የማይጠገን አደጋ ዉስጥ መዉደቁ አይቀርም።

ይህ የአገራችን አንድነት አደጋ ላይ የመዉደቁ ዜና እጅግ በጣም የሚያስፈራና የሚያሳዝን ዜና ነዉ። ደግነቱ የሚያስደስተን፤ ተስፋችንን የሚያለመልምና አንገታችንን ቀና የሚያሰደርግ ዜናም አለ። ወያኔ አገራችን ላይ ይዞት የመጣዉ አደጋ ከወዲሁ የታያቸዉ ኢትዮጵያዉያን የአባቶቻችዉን ፈለግ ተከትለዉ ዱር ቤቴ ብለዉ ወያኔን በሚገባዉ ቋንቋ ለማነጋገር ተዘጋጅተዋል።የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔንና ወያኔ የፈጠረዉን ዘረኛ ስርዐት ደምስሶ ፍትህ፤እኩልነትና ነጻነት የሰፈነባትን ኢትዮጵያ ለመገንባት በሚየደርገዉ ትግል የመጀመሪያዉ ምዕራፍ ዉስጥ እንደ ኤርትራ ህዝባነ መንግስት አጋር ሆኖ የተሸከመዉ ሌላ አገርም መንግስትም የለም።የኤርትራ ህዝብና መንግሰት ወያኔ የሚባል ነቀርሳ ከስሩ እስካልተነቀለ ድረስ የአፍሪካ ቀንድ የሰላም አየር እየተነፈሰ በሠላም መኖር እንደማይችል ከተረዱ ቆይተዋል። ስለዚህም ነዉ የኢትዮጵያን ህዝብ የነጻነት አርበኞች አስጠግተዉ አስፈላጊዉን እርዳታ ሁሉ የሚያደርጉላቸዉ። ዛሬ ኢትዮጵያንና ኤርትራን የሚመሩ መሪዎችና መንግስታት ዘሏአለማዊ አይደሉም፤ የሁለቱ አገሮች ህዝብ ወንድማማችነትና ጉርብትና ግን ዘለአለማዊ ነዉ። በዚህ ዘሏአለማዊ ወዳጅነትና ጉርብትና ዉስጥ የስግብግቦቹ የወያኔ መሪዎች አመለካከት "እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል" ካለችዉ እንስሳ የሚለይ አይደለም።ከፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ቃለመጠይቅ በግልጽ እንደሰማነዉ በኤርትራ በኩል ያለዉ አመለካከት ለኢትዮጵያነ ለኤርትራ ህዝብ ታሪካዊ ትስስር፤ ጉርብትናና ወደፊት ወዳጅነት እጅግ በጣም ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ አመለካከት ነዉ። አርበኞች ግንቦት ሰባትና የኤርትራ መንግስት በኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝብ የተሳሰረ የጋራ ዕድገት፤ ብልጽግናና መልካም ጉርብትና ላይ እንደ ነቀርሳ የተተከለዉ ዘረኛዉ የወያኔ ስርዐት ነዉ ብለዉ ያምናሉ። ይህ ነቀርሳ በተባበረ የህዝብ ትግል መነቀል አለበት ብለዉም ያምናሉ።

.... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## በጄኔቫ የሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ "የተቃዋሚ ደጋፊዎች ናችሁ"ያላቸውን ኢትዮጲያውያን ፓስፖርት አላድስም አለ

አገር ዉስጥ "ወርቃማዉ ዘር"፤ "ልማታዊ አርቲስትና" "የፓርቲ አባል" እያለ ዜጎችን በደረጃ ከፋፍሎ የሚመለከተዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ይህንን ከፋፋይ ስርዐቱን በዉጭ አገሮችም በተለይ በሚቆጣጠራቸዉ ኤምባሲዎቹ ዉስጥ ሲያካሄድ መቆየቱ የሚታወስ ነዉ። በትግርኛ ተናጋሪዎችና በታማኝ ባንዳዎች የተሞላዉና የበየአገሮቹ የሚገኘዉ "የኢትዮጵያ ኤምባሲ" ለኢትዮጵያዉያን ምንም አይነት አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የተገልጋዩን ኢትዮጵያዊ የብሄር ማንነት በተለይ ግለሰቡ የስርዐቱ ደጋፊ መሆኑን ሳያጣራ ምንም አይነት አገልግሎት እንደማይሰጥ ይታወቃል።

በቅርቡ ስዊዘርላንድ የዙሪክ ዉስጥ ነዋሪ የሆኑትና የሰብዓዊ መብት ተሚጋች የሆኑት ወይዘሮ ፊዮሬላ ሮማኖ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ለኢሳት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ እንደገለጹት ፓስፖርታቸውን ለማሳደስ ቀጠሮ አስይዘው ከሚኖሩበት ከዙሪክ ከተማ ኤምባሲው ወደሚገኝበት ጄኔቫ የ3 ሰዓት መንገድ ተጉዘው ቢሄዱም፣ የኤምባሲ ሰራተኞቹ በአካል ሲያዩዋቸው በተቃውሞ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ መሆናቸዉን ስላወቁ ግለሰቧ የጠየቁትን አገልግሎት ሳይሰጡ መልሰዋቸዋል።ኤምባሲው እንደደረሱ ኀይቶአም በሚባል ሰራተኛ የተሰጣቸውን ፎርም ከሞሉና ፎቶግራፋቸውን ከሰጡ በሁዋላ በስዊዘርላንድ ለምን ያህል ዓመት እንደቆዩ ጥያቄ የቀረበላቸው ወይዘሮ ፊዮሪና፣ ለ13 ዓመት መቆየታቸውን ሲናገሩ፦" በ 13 ዓመታት ውስጥ ለሀገርዎ ምን ሰሩ?" የሚልና ከፓስፖርት እድሳቱ ጋር ተያያዥነት የሌለው ተጨማሪ ጥያቄ እንደቀረበላቸው ተናግረዋል። ለቀረበላቸው ጥያቄ በደፈናው፦"እሱን ሀገሬ ስሄድ የማምንበትን ጉዳይ አፈጽማለሁ" የሚል ምላሽ መስጠታቸውን የገለጹት ወይዘሮ ፊዮሪና፣ ይኼኔ ፦"አንቺን በደንብ እናውቅሻለን፤ ለጊዜው ፓስፖርት ማደስ አቁመናል" እንደሏቸው ገልጸዋል። ቀጠሮ አስይዤ ደርሶ መልስ የ6:00 ሰዓት መንገድ ተጉዘው ከመጡ በሁዋላ የዚህ ዓይነት ምላሽ በማግኘታቸው የተበሳጩት ወይዘሮ ፊዮሪና፣ በጊዜው ኤምባሲ ለመሄዳቸውና የፓስፖርት እድሳት ጥያቄ ለማቅረባቸው ማረጋገጫ ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ቢጠይቁም ኤምባሲው በእምቢተኛነቱ መጽናቱን ገልጸዋል።

ወይዘሮዋ ጉዳዩን ለስዊዘርላንድ ፖሊስ አመልክተዉ የማመልከቻዉን የፖሊስ የማረጋገጫ ወረቀትና ፊርማ ይዘው ወደ ኤምባሲዉ ተመልሰው "መንግስትን መቃወምም ሆነ መደገፍ መብት እስከሆነ ድረስ ከኤምባሲ አገልግሎት እንዳናገኝ ምክንያት ሊሆን አይችልም" ብለው ሲናገሩ "እሱን ሄደሽ ኢሳት ላይ ተናገሪ" እንደተባሉ ተነናግረዋል። ወይዘሮ ፊዮሪና፤ በተቃውሞ ሰልፎች በመሳተፋቸውና የኢሳት ደጋፊ በመሆናቸው ከኤምባሲው አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸውን በዝምታ እንደማያልፉት ተናግረዋል። "እኔ ብቻ ሳልሆን በርካታ እንደኔ ያሉ ህጋዊ ነዋሪዎችም ተመሳሳይ ችግር እየደረሰባቸው ነው" ያሉት ወይዘሮ ፊዮሪና፤ ከሀገራችን ተሰደን እዚህም ሁለተኛ ስደተኛ መሆን ስለሌለብን የኔ ዓይነት ተመሳሳይ ችግር ከደረሰባቸው ወገኖቼ ጋር በመሰባሰብ በኤምባሲው ላይ ተከታዩን ህጋዊ እርምጃ ለማስወሰድ ተዘጋጅተናል ብለዋል። ወይዘሮ ፊዮሪና ፦"ኤምባሲው ለኢትዮጵያውን በእኩልነት አገልግሎት መስጠት ካልቻለና የቤተሰብ ኩባንያ ከሆነ እኛ ባለንበት ሀገር ሊኖር አይገባም"ያሉት ወይዘሮ ፊዮሪና፤ ኢትዮጵያውያን ያለምንም ፍርሀት ተባብረን ልንነሳ ይገባል ብለዋል። ወይዘሮ ፊዮሪና ሀሳባቸውን ሲያጠቃልሉም እኔን ኢትዮጵያዊ ያደረገኝ ጥንት አያቶቼ የከፈሉት የደም መስዋእትነት እንጂ ትናንት የመጣ ወያኔ አይደለም "ብለዋል።

## የዉጭ ጉዳይ ሚ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም አሁንም ቅሌት ዉስጥ ገባ

ከዚህ ቀደም የወያኔ አገዛዝ ዜጎቹ መሆናቸዉን ረስቶ ሳዑዲ ዉስጥ ከፍተኛ ችግር፤ስቃይና ድብደባ የደረሳባቸዉን ኢትዮጵያዉያን "የኢትዮጵያ መንግስት" እረዳና ወደ አገ ራቸዉ እንዲመለሱ እያደረገ ነዉ ሲል ትልቅ ዉሸት የዋሸዉ ቴዎድሮስ አሁን በቅርቡ ደግሞ ያልነበረና የሌለ ነገር ፈጥሮ መዋሸቱንና በተለይም ታዳጊዋን ወጣት በብሄራዊ ደረጃ እንድትዋሽ ማድረጉን አገር ዉስጥና የዉሸቱ መሠረት በሆነችዉ አዉስትራሊያ ዉስጥ የሚገኙ ምንጮች ገለጹ። ቴዎድሮስ አድሃኖም ላለፉት ሃያ አራት አመታት የዋሸዉ ዉሸት አልበቃ ብሎት ወጣቶችን ዉሸት ማስተማሩ ብዙ ኢትዮጵያዉያንን አስቆጥቷል።

ብሪቱ አህመድ የምትባለዉንና ሜልቦርን በሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት በመማር ላይ የምትማር ወጣት ለአገሯ 20 ሚሊዮን የአዉስትራሊያ ዶላር አስገኘች ብሎ ወጣቷን በየማህበራዊ ሜድያ ላይ ያቀረባት ቴዎድሮስ አድሃኖም ዉጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ የዜና አዉታሮች ተጠይቆ ስለ ጉዳዩ ለመናገር ፈቃደኛ አልሆነም። ሆኖም ዜናዉን በኢቲቪና በማህበራዊ ሜድያዎች የተከታተሉ አያሌ ኢትዮጵያዉይን ሽልማቱን ሰጠ ወደተባለበት ተቋም ስልክ ደዉለዉ ባገኙት መራ መሰረት ተቋሙ ስለሽልማቱ ምንም የሚያዉቁ ነገር እንደሌለ ገልጿል።

ይህ እንዳልተገለበጠ ቂጣ ግማሽ ጥሬ ግማሽ ብሰል የሆነ ዜና አንዳንድ እዉነቶች ቢኖሩትም የዜናዉ አንኳር የሆነዉ የ20 ሚሊዮኑ ዜና ግን የተለመደ የወያኔ የፈጠራ ዉሸት መሆኑን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ። በእርግ የመማር ዕድል ያላገኙት ወላጅ እናቷና ከዘጠነኛ ክፍል ሊዘልሉ ያልቻሉት የአባቷ የትምህርት ሁኔታ የሚያስጨንቃት ወጣት ብሪቱ አህመድ አዉስትራሊያ ዉስጥ በትምህርት ላይ ትገኛለች፤ በአንዳንድ የትምህርት ቤቱ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይም ትሳተፋለች። ሆኖም ወጣቷ ባደረገችዉ ተሳትፎና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ባደረገችዉ ዉድድር አሸንፋ 20 ሚሊዮን የአዉስትራሊያ ዶላር አገኘች የተባለዉ ዜና በፍጹም ሊረጋገት አለመቻሉንና ሽልማቱን ሰጠ የተባለዉ ተቋም አመታዊ የመተዳደሪያ በጀቱ ሰጠ ከተባለዉ ሽልማት በእጥፍ እንደሚያንስ ለማረጋገጥ ተችሏል። ባጠቃላይ አገር የመምራትና ወጣቱን ትዉልድ በስነስርዐትና ሞራል አንፆ ማሳደግ የሚገባዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም ወጣቷም ኢትዮጵያም ያላገኙትን ገንዘብ ወጣት ብሪቱ አህመድ የተሸለመችዉን ሃያ ሚሊዮን የአዉስታራሊያ ዶላር ለህዝብና ለአገር ሰጠች ብሎ ጥልቅ ዉሸት ሲዋሽ እጅ ከፍንጅ ተይዟል።

## የፖለቲካ አመለካከታቸዉ ከህወሓት የተለየ የትግራይ አርሶ አደሮች የመስኖ ውሃ እንዳይጠቀሙ ተደረጉ

በአጽቢ ወንበርታ ወረዳ በሩባ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ በርካታ ቁጥር ያላቸው አርሶ አደሮች ለኢሳት እንደገለጹት፣ የአረና ፓርቲ አባላት ናቸው በሚል የመስኖ ውሃ እንዳያጠጡ በመከልከላቸው፣ ሰብሎቻቸው እየደረቁ ነው። 12 አርሶ አደሮችን በመወከል ለኢሳት የተናገረው አቶ ህድሮም ሃይለስላሴ የተቃዋሚ አባላት ብቻ በመሆናችን አትክልቶቻችንን የመስኖ ውሃ እንዳያጠጡ፣ ከእነሱ መካከል ሁሉቱ ብቻ የተቃዋሚ አባላት ቢሆኑም፣ ዘመዶቻቸው ሁሉ ተክሎቹን ውሃ እንዳያጠጡ እንደተከለከሉ ተናግረዋል። ከፓርቲው ከወጣችሁ ውሃ የማጠጣር ፈቃድ ታገኛላችሁ መባላቸውን የሚናገሩት አቶ ህድሮም፣ በአቋማቸው በመጽናታቸውና ፈቃድ በመከልከላቸው በተለይ ቋሚ ተክሎች እየጠወለጉ መሆኑን አክለዋል።

ህወሃት 40ኛ አመቱን ሲያከብር ለክልሉ ልማትና ዲሞክራሲን ማምጣቱን ተናግሯል፣ እርስዎ ደግሞ ችግር አለ ይላሉ ተብለው የተጠየቁት አቶ ህድሮም፣ ህወሃት በደርግ ጊዜ የተቀበሩ አስከሬኖችን ሲያወጣ ፣ አሁን ያለውን ህዝብ ግን በቁሙ እየቀበረው ነው የሚል መልስ ሰጥተዋል። የትግራይ አርሶአደር በማዳበሪያ እና በሌሎችም እዳዎች በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንደሚገኝና የቻለው ወደ አረብ አገር እየተሰደደ መሆኑን አክለዋል። በተመሳሳይ ዜናም በትግራይ ከፍተኛ የዘይት እጥረት መፈጠሩንና ህዝቡ ዘይት ለማግኘት ረጅም ሰልፎችን መጠበቅ ግድ እንደሚለው መረጃዎች አመልክተዋል።

## የአድዋ ድል በአል በተለያዩ የአለም

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ለመግዛት የመሠረተ ዲንጋይ ያኖረበትን አርባኛ አመት በሙቶ ሚሊዮኖች ብር አያወጣ ሲያከብር በአንጻሩ ኢትዮጵያንና ህዝቧን ከጣሊያን ኢምፔሪያሊዝም የጋረደዉን ታላቁን የአድዋ በዐል እንደተራ ቀን ሲያልፈዉ ሞክሯል። በተለይ በዐሉ አዲስ አበባ ዉስጥ በሚከበርበት ወቅት የአባቶቻቸዉን አንፀባራቂ ድል በጭፈራና በሽለላ ለማክበር የሞከሩ ወጣቶችን የወያኔ ፖሊሶች ጣልቃ ገብተዉ ሲከለክሉ ታይተዋል። ህዝብ ሲደሰት፤ ታሪኩን ሲዘከርና ኢትዮጵያዊነቱን በተለያዩ መንገዶች ሲገልጽ ደማቸዉ የሚፈላ የወያኔ መሪዎች ባለፉት ሃያ አራት አመታት ህብረተበሱን በተለይ ወጣቱን ሲያስሩ፤ ሲደብቡ፤ ሲደግሉና ከአገር እንዲሰደድ ሲያደርጉ መቆየታቸዉ የሚታወስ ነዉ።

### የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጀል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ እንደ ዕቃ የሚጠቀምበትን ሠራዊት አወደሰ

የዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ምረዎችና ካድሬዎች ህወሓት በአንድ ዘር የበላይነት ላይ መስርቶ ላራሱ ጥቅምና ኢትዮጵያዊያንን አንገት አስደፍቶ ለመግዛት የሚጠቀመበትን ሠራዊት የህዝብ ወገንና ልማታዊ ሠራዊት እያሉ የዉሸት ዉዳሴ ሲሰቱት መዋላቸዉን አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። የሰራዊቱ ከፍተኛ መኮንኖች እና መንግስት ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በተደረገው የምስጋና ሲምፖዝየም በከተማዋ ከሚገኙ ክፍለ ከተማዎች የተመረጡ የገዢው ፓርቲ አባላትና አቀንቃኞች እንዲሁም ከየመምርያው የተወከሉ አባላት በተገኙበት መከላከያ ሰራዊቱ ለሃገሪቱ ዘብ የቆመ፣ በልማቱ ተሳታፊና ሁለንተናዊነቱን በማንሳት መወድሰ- መከላከያ ሰራዊት ሲደረግ ውሎአል።በዚህ የሰራዊቱን አመራሮች የማድነቅ ስነስርዓት ላይ ንግግራቸው በጭብጨባ እንዲታጀብ እጠየቁ ተሰብሳቢውን ሲያነቃቁ የነበሩ አንድ ሴት በንግግራቸው መካከል ነገር አሳመርኩ ብለው ያልተጠበቀ ነገር ተናገሩ።

እኝህ እናት ከፊት ለፊት የተደረደሩትን ባለስልጣናት በመመልከት “ዛሬ ያለው ውጊያ ከድህነት ጋር ነው፣ሀገራችን ከበለጸጉ ሀገሮች ጋር እኩል ሆና ሀገራችንን እንደምናያት ርግጠኛ ነኝ።” አሉ፣ ቀጡለና በዚህ ስርዓት የሴቶች መብት ተከብሯል ፣የመናገር መብት ተከብሯል። የነበረውን ስርዓት እናውቀዋለን ካሉ በሁዋላ የቀድሞውን ስርአት ወደ መግለጽ ገቡ። በቀድሞው ስርዓት ስኳር በግድ ውሰዱ ተብለን እንቀጣ ነበር፣ አሁን ግን ብለው ሲናገሩ ባለስልጣናቱ ራሳቸው ሳቃቸውን መቆጣጠር ተሳናቸው አንደነበርና ነገር አሳመርኩ ያሉት ተናጋሪም በድንጋጤ ነገሩን ለማድበስበስ ሲሞክሩ ተሰብሳቢውን የበለጠ አስቀዉታል።

## ሶስት ሚሊየን ብር የሚጠጋ ወጭ የወጣበት ድልድይ የጥራት ችግር አለበት ተባለ

በአባይ ወንዝ ላይ የተሰራዉ 108 ሜትር ርዝመት እና አንድ ነጥብ ስድስት ሜትር ስፋት ያለው ተንጠልጣይ ድልድይ በሃገሪቱ ብቸኛዉ የተንጠልጣይ ድልድይ በመስራት በሚታወቀው ሄልቬታስ ሲዊዝ ኢንተርኮኦፕሬሽን በተሰኘ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ባለፈው ታህሳስ ወር መጨረሻ በይፋ ተመርቆ ስራ ቢጀምርም፣ በምረቃው ስነስርዓት የተገኙ ባለሙያዎች ድልድዩ የጥራት ችግር እንዳለበት መናገራቸው ነዋሪዎችንና በቦታው ተገኙ አመራሮችን አስደንግጧል።

በአማራ ክልል ገጠር መንገድ ስራዎች ድርጅት የቁጥጥርና ክትትል ኬዝ ቲም ባለሙያ የሆኑት አቶ ይገርማል ታምር በዝርዝር ያቀረቡት የጥራት ችግር በምረቃ ስነስርዓቱ ለታደሙ የክልል እና የባህርዳር ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ኃለፊዎች፣ ግንባታውን በኃላፊነት የሰራው ባለሙያ እና የአካባቢውን ነዋሪዎችን ያስደነገጠ እንደነበር በምረቃው ስነስርዓት የተገኙ ታዛቢዎች ተናግረዋል። 40 በመቶ በሄልቬታስ፤ 60 በመቶዉ ደግሞ ከዓለም ባንክ የግብርና እድገት ፕሮግራም በተገኘ ገንዘብ ወጭዉ የተሸፈነው ይህ ድልድይ ለሃምሳ አመታት እንዲያገለግል ታስቦ የተሰራ ቢሆንም የተሰራበት የድንጋይ አይነት፣የውሃ አጠጣጡ እና ገመዶችን ወጥሮ የያዘው የግንባታ አካል ስጋት ያለበት መሆኑን ባለሙያው ተናግረዋል።

የዳስራ ማርያም እና የጭስ አባይ እንዲሁም በደቡብ ጎንደር ዞን ደግሞ የደራ ወረዳ የተወሰኑ የገጠር ቀበሌ ነዋሪ አርሶ አደሮችን የዘመናት ጥያቄን የፈታ ሁኗል የተባለለት ታንኳ በር ተንጠልጣይ ድልድይ እንዲሰራ ላለፉት ሁለት ዓመታት አርሶ አደሮች በተደጋጋሚ ለሚመለከተዉ አካል ጥያቄ ሲያቀርቡ ቆይተዋል። ሄልቬታስ ስዊዝ ኢንተርኮርፕሬሽን የተባለው የግብረ ሰናይ ድርጅት በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች የሚሰራቸውን ተንጠልጣይ ድልድዮች ስራ በብቸኝነትና ማንም ተቆጣጣሪ በሌለበት ሁኔታ እንደሚሰራና ማኔጅመንቱም በአንድ አካባቢ ሰዎች ብቻ የተያዘ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ድርጅቱ በአምስት ክልሎች ከስልሳ በላይ ተንጠልጣይ ድልድዮችን እንደሰራ በእለቱ የምረቃ ስነስረአት ላይ ተገልጿል።

## ወያኔ በምርኮኛ ወታደሮች የመሰረተው ኦህዴድ 25ኛ ዓመቱን

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

የቀድሞ የህወሓት ከፍተኛ አመራርና ታጋይ የነበሩት አቶ ገብሩ አስራት በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፍ ህወሓት በጫካ በነበረበት ወቅት እንደአነግ ካሉ የኦሮሞ ድርጅቶች ጋር ግንባር ለመመስረት የነበረው ፍላጎት ባለመሳካቱ ይህንን ክፍተት ለመሙላት በሻዕቢያ ተማርከው መንገድ ሲያሰራቸው የነበሩትን የኦሮሞ የቀድሞ ወታደሮችን ወደ ማሰባሰቡ ፊቱን ማዞሩን አስረድተዋል። እነዚሁ ምርኮኛ የቀድሞ መንግስት ወታደሮች አንዳንዶቹ ኢህዴን እየተባለ በሚጠራው ድርጅት ታቅፈው እንደነበርም ያስታወሱት አቶ ገብሩ፣ እነዚህኑ ንቁና ዝግጁ የሆኑ ወታደሮች በማሰባሰብ የህወሓትን ፕሮግራም በመያዝ በ1982 ዓ.ም ሰሜን ሸዋ ውስጥ ደራ አካባቢ ኦህዴድ መመስረቱን አስታውሰዋል። ኦህዴድን በማቋቋም ረገድ ግንባር ቀደም ከነበሩት መካከል ኩማ ደመቅሳ በቀድሞ ስሙ ታዩ በአሁኑ ወቅት በአምባሳደርነት የተሾሙ፣ ኢብራሂም መልካ ከድርጅቱ ተሰናብተው ነጋዴ የሆኑ፣ አባዱላ ገመዳ የፓርላማ አፈጉባዔ የሆኑ፣ ባጫ ደበሌ የመከላከያ ጄኔራል የነበሩና በአሁኑ ወቅት በጡረታ ላይ የሚገኙ የሚጠቀሱ መሆናቸውን አቶ ገብሩ “ሉአላዊነትና ዴሞካራሲ በኢትዮጵያ” በሚል ስም በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፋቸው ገልጸዋል። ህወሓት የተመሰረተበትን 40ኛ ዓመት በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በመከስከስ ከአንድ ወር በላይ ሲከበር የቆየ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የኦህዴድ 25ኛ ዓመት በዓል ከፍተኛ ገንዘብ ፈሶበት እንዲከበር የተወሰነው እግረመንገድ አጋጣሚውን ለምርጫ ቅስቀሳ ለመጠቀም እንደሚመች መሆኑ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች እየተናገሩ ነው። ይህ በመንግስት ሐብትና ገንዘብ ለአንድ ፓርቲ የሚደረግ የምርጫ ቅስቀሳ ሕገወጥ መሆኑንም እነዚሁ ምንጮች ይገልጻሉ።

## ሱዳናዊዉ ሹፌር በጨቤ ወግቶ ከመኪና የወረወራት

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ድርጊቱን በጭምጭምታ የሰሙት የሃሙሲት ከተማ ነዋሪዎች ድንጋይ ደርድረው የመኪናውን መምጣት ሲጠባበቁ ይቆያሉ። ሹፌሩ ተረጋግቶ ሃሙሲት ሲደርስ ነዋሪዎች አውርደው መደብደብ ይጀምራሉ። ፖሊሶች በመሃል ገብተው የሹፌሩን ህይወት ካተረፉ በሁዋላ፣ ወዲያውኑ የደህንነት ሃይሎች ሹፌሩን ወደ ወረታ ከተማ ወሰዱት። የሹፌሩ መወሰድ ያበሳጫቸው ነዋሪዎች ፣ፖሊስ ጣቢያውን በመክበብ “በሰው አገር እየሞትንና እየተዋረድን ባለበት ሰአት በአገራችንም እንዲህ የምንሆን ከሆነ፣ ከባርነት የባሰ ኑሮ ነው የምንኖረው” በማለት ቁጣቸውን ሲገልጹ አርፍደዋል። ነዋሪዎች በሱዳንና በኢህአዴግ መንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት በመጥቀስ ሹፌሩ ይለቀቃል የሚል ስጋት እንዳላቸው ተናግረዋል። የወጣቱዋን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ ያደረግነው ጥረት አልተሳካም። ይሁን እንጅ የአይን እማኞች የደረሰባት አካላዊ ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን በመጥቀስ ላትተርፍ ትችላለች በማለት ስጋታቸውን እየገለጹ ነው። ሱዳናዊው አሽከርካሪ ያለበትን ሁኔታ ለማጣራት ያደረግነው ሙከራም አልተሳካም።

## የኢትዮጵያ ጠላት ወያኔ - ወያኔ ብቻ ነዉ! ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

“አህያዉን ፈርቶ ዳዉላዉን እንዲሉ” ዛሬ ወያኔ “ኤርትራ” “ኤርትራ” እያለ የአዞ የሚያነባዉ እሱ ባልተገራ አንደበቱ ሊነግረን እንደሚፈልገዉ ኤርትራ በእርግጥም የኢትዮጵያ ጠላት ሆና አይደለም። ጉዳዩ ወዲህ ነዉ። ወያኔ በኤርትራ አሳብቦ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነጻነት የቆሙ ኃይሎችን ቆርጦ ተነስቷል፤ ይህንን ለማወቅ ደግሞ ብዙ መረጃ መሰብሰብ አያስፈልግም። እራሳቸዉ የወያኔ መሪዎች በየመድረኩ የተናገሩትንና ቡችሎቻቸዉ ደግሞ በቅርቡ አዲስ ዘመን ላይ የጻፉትን ጽሁፍ ማንበቡ ይበቃል - እንዲህ ሲሉ ነበር የጻፉት “አለም አቀፍ ሕጉን ማክበር በሚል እንጂ ዛሬ ይህንን ደባና ሴራውን በጣጥሦ በመጣል ከነሎሌዎቹ ድባቅ በመምታት ከነበረ ወደአልነበረ በመለወጥ ያለአንዳች እንቅፋት ይሕንን ዘመን የማይሽረው ጻረ ኢትዮጵያ ሀይል ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና እፎይታ ማስገኘት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ ቆርጣ ስትነሳ የሚገታት አንድም ሀይል የለም” የኢትዮጵያ ወጣት፤ ሠራተኛ፤ ገበሬ፤ የመከላከያ ሠራዊት አባላትና ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ወያኔ ምን ያህል አንተንና አገርህን አንደሚጠላ ባለፉት ሃያ አራት አመታት በግልጽ አሳይቶሀል። ዘንድሮ ደግሞ በተለይ ባለፉት ሦስት ሳምንታት አንተና ልጆችህ በየቀኑ እያደገ በሚሄደዉ የኑሮ ዉድንት እየነደዳችሁ ወያኔ ግን አገራችንን በዘር ከፋፍሎ ለመግዛት የመሠረት ዲንጋይ ያኖረበትን ቀን ለማክበር ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር በላይ አባክኗል። ከዚህ በተጨማሪ ነብሰ ገዳይ ፖሊሶቹን አሰማርቶ አባቶችህ አድዋ ላይ ያጎናፀፉህን አንጸባራቂ የጥቁር ህዝብ ድል በሆታና በእልልታ እንዳታከብር አድርጓል።

ባጠቃላይ አርባኛዉ አመት የህወሓት ምስረታና የኢትዮጵያ ህዳሴ የሚል አዲስ የመላምት ታሪክ እንዲጻፍ እያደረገ በአባቶችህና በእናቶችህ ደም የደመቀዉን ትልቁን የአድዋ ድል ታሪክ እንዲደበዝዝ አድርጓል። የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋ ነዉ - በእርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋ ነዉ። ኢትዮጵያዉያን ታጋሾች ናቸዉ? ያለምንም ጥርጥር ኢትዮጵያዉያን አለም የሚያዉቃቸዉ ታጋሾች ናቸዉ። ነገር ግን ትዕግስትም ሆነ ጨዋነት ትርጉም የሚኖራቸዉ ህዝብ መብቱና ነጻነቱ ተከብሮ በማንነቱ ኮርቶ መኖር ሲችል ብቻ ነዉ። እየተረገጠ፤ ልጆቹ ከጉያዉ እየተወሰዱ እየተረሸኑና ታሪኩ ፤ አንድነቱና ብሄራዊ ማንነቱ ሲዋረድ የሚታገስና አንገቱን ደፍቶ የሚኖር ህዝብ የለም። በሳምንቱ መግቢያ ላይ ያከበርነዉ የአድዋ ድል በዐልም የሚያሳስበን ይህንን እዉነት ነዉ። የዚህ ዘመን ኢትዮጵያዊ አባቶቹና እናቶቹ በነጭ ፋሺስቶች ላይ በተጎናፀፈት የአድዋ ድል መኩራት ብቻ ሳይሆን የሱም ልጆች አባቶቼ ብለዉ አንዲኮሩበት የአድዋን ድል በዛሬዎቹ ጥቁር ፋሺስቶች ላይ መድገም አለበት። አድዋ የእኛ የኢትኦጵያዉያን ብቻ ሳይሆን የአለም ጥቁር ህዝብ በነጭ ወራሪዎች ላይ የተጎናፀፈዉ አንፀባራቂ ድል ነዉ። አድዋ ትዕግስትና ጨዋነት ለማይገባቸዉ እብሪተ ችና ትዕቢተኞች ቆራጡና ጀግናዉ የኢትዮጵያ ህዘብ የማይረሳ ትምህርት ያስተማረበት ቦታ ነዉ። ዛሬ ደጃፋቸዉ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ የሰራዉን ገድል የረሱና አድዋ ላይ ታሪክ ሲሰራም ቢሆን ባንዳዎች የነበሩ የባንዳ ልጆች ከቅኝ ገዢዎች ባልተለየ ጭካኔ፤ ዝርፊያና ጥላቻ አገራችን ኢትዮጵያን እንዳልነበረች እያደረጓት ነዉ። የዛሬዉ ትዉልድ ኢትዮጵያዊ ከዚሁ ከአድዋ አፈር በቅለዉ በራፋቸዉ ላይ ህዝብ የሰራዉን ታሪክ እየፋቁ የራሳቸዉን የመላ ታሪክ የሚጽፉ ከዲዎችን አባቶቹ ለፋሺስቶች ያስተማረዉን ትምህርት ለነዚህ ፋሽስቶችም እንደገና ማስተማር አለበት።